# ጅቡ መጣ…!!? ና

# የቃሊቲ ፍርድ ቤት!!

**አስፋ ጫቦ Dallas ,Texas,USA**

*የቦንቡ ፍንዳታ ብዛት አንዳንድ ነገር አስታዋሰኝና  እስቲ መላ ያለው መላ- ምት ልሞክር ብየ ነው። ክኔ የሚሻሉ ለያሰስፉት ሊያስፋፉት ይችላሉ ብየ አስባለሁ። ቢደርጉ ደስ ይለኛል። አንድ ልብ ካላልነው ውስጥ ሊሆን ይችላል።*

*ወያኔ አዲሳባ ሲገባ  እዚያው አዲሳባ  ነበርኩ።ያውም አራት ኪሎ።ቤቴ ቀድስት ማርያም ጎን ካሉት መንታ ፎቆች (Twin Towers) በማርያም በኩል ያለው ነበር። 14ኛው ፍቀ (የመጨረሻው) ላይ ነበርኩ። ከዚህ የተነሳ ጣራውም የኔ ነበር፤ ይህ ማማ (ጣራ) ሩቀ ያሳያል። ዝቋላና የረር  ጋራ ተግ በለው ይታያሉ። እይታው አሁን ከምናገረው/የምጽፈው ጋር የሚሐድልኝ  ሆኖ ነው የማነሳው። የትዝታ ፈለግ…የመራራ ትዝታ ፈለግ… መሆኑ ነው፤*
*ያኔ ፥የዚያን ስሞን ከሁኑት ነገሮች ውስጥ  ጎልተው እንደስእል በአይነ ሒሊና የሚታዩኝ ጥቂት ዛሬ ማንሳት ፈልግሁ። ካሁን ቦንቡ ፍንዳታ ጋር የሚገናኙትስለማሰለኝ። ነው።*

1. *አንዱማንሳት የፈለግሁት  ከስሜን ጦር ግንባር ወደአዲስ አበባ የሚጎረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት ሁኔታ ነበር። ወያኔ አዲስ አበባ  ከማግባቱ በፊት በነበረው አንድ ሳምንትና እንዲያ  ውስጥ በሽህ የሚቆጠር ሠረዊት ሙሉ የጦር መሳሪያውን እንደታጠቀ ወደአዲሳባ ጎረፈ። የተራበ ፥ የተጠማ ብቻ ሳይሆን ሞራሉ የተነካ ጭምር መሆኑ ካካሄዱ ከቁማናውና ከገጽታው   ጭምር* (body language) *መገምት ይቻላል ። ይታያልም። ሞራሉ ለምንና እንዴት ተነካ የሚለውን ሌላ ጊዜ አንስቼው የነበረ ቢሆንም አንድ ቀን መመለሴ አይቀረም።*
2. *እጅግ የሚገርመውና  የሚያስደንቀው(ሌላው ቢቀር ለኔ) ያ እንዲያ መሳሪያ የታጠቀው ወታደር የሚበለውና የሚጠጣጣው አጥቶ   ወይ ለምኖ ወይም ሰብአዊያን  ሰጥተውት ወይም መሳሪያን ሸጦ ነበር።እንዲህ መሳሪያ የታጠቀ ተስፋውን የቀረጠ ወታደር ለምኖ ወይም ገዝቶ ሲበላ በታሪክ የመጀመሪያው ነው የሚሰኝ ጥናት ባይኖረኝም እኔን እስከውዲያኛው  የሚገረመኝ፥ እንዳከበረው ያደረገኝ ነጥብ ነበር።*
3. *ያ ባይሆን ኖሮ መሳሪያ መጠቀም መቀማት መዝርፍ  የራሱን ፍላጎት ማርካት ብቻ ሳይሆን ለውያኔ ዘረፋ በሩን ወለል አድርጎ ይከፍት ነበር ማለት ነው። ይቅርታ! ከዘረፈው በላይ ዘርፉ ለማለት ነው።  ወያኔ  ቃታ ለማሳብ፥ለማፈንዳት በቋፍ ላይ ሰበብ አስባብ የይፈልግ ነበረና ነፈጉት። ሕዝብ በተከማተቸበት አዲሰ አበባን በመስለ ከተማ “ጎሮ ወሾባየ…” ብለው ለመግባት ሲቋምጡ ወያኔን ሰብብ አስባብ ነሳቸው። ከዚህም ሌላ ፥በነጋታው በሰልስቱ በሳምንቱ በኖ ትኖ ጠፋ። ከህዝብ ጋር ተቀለቀለ። ተጠራቅሞ ተስባስቦ ቢገኝ ኖሮ ህዝቡን ለመምታት ለላ ስበብ ይፈጥር ነበርና ነው። ሰበቡን ነሱት። በዚህ የካሱን ይመስለኛል፤5 ምን አንደበደሉን ግን እርግጠኛ አይደለሁም። እንዲህ ሲሆን  ጊዜ ሰበብ- አልባ መአት  አወረዱብን።*

4. በስኔ ወር 1982 ፥አንድ ምሽት፣ ከምሽቱ ምናልባት ወደ አራት ሰአት ቤታችን ተናወጸ።ተናወጸ ለስላሳ ቃል ነው። ግን ሌላ ገላጭ ቃል ማግኘት የማልችል ስለመሰለኝ ነው። ወይም፣ አንድ ከባድ፣ የተቀጣ ምድራዊና ስብአዊ ያልሆነ ኀይል ቤታችንን በቁጣ ነቅንቆ፣ ከስሩ መንግሎ፦ ግራ ቀኝ ወዝውዞ መልሶ እንበረበት በቁጣ የወረወረ ነበር የሚመስለው/የተሰማኝ። ወይም ብትንትኑን ለማውጣት አሽቀጥሮ ጥሎት ህንጻው አንድ በራሱ ባልተወቀ ኀይልና ምክንያት ብትንትኔ አይውጣም ብሎ ተመልሶ ቦታው የተቀመጠ የሚመስል ነበር። መኝታ ቤታችን አስፈሪ አስደንጋጭና በሚለዋወጥ ብባለ ብዙ ቀለማት ብርሐን ተዋጠ። የነብረነው በሙሉ በድንጋጤና በብርክ ጮኽናል። የጮህን ይመሰለኛል። ከውጭ የሚስማ ምድራዊ ያለሆነ ከፍተኛና ተከታታይ የሆነ ድምጽ ስለነበረ "ጮኼናል" የምለው መጮህ ነብረብን ከሚል ነው እንጅ ከውጭ ባለው ድምጽ ምድር ሁሉ የተዋጠ ። ስለነበረ መስማትና/መሰማማት የሚቻል አልነበረም።
5. አድሮ እንደተስማው <u>ይህ የጥይት ቤቱ ፍንዳታ መሆኑ ነው።</u> እዚሁ አራት ኪሎ ቤት መንግስቱ ሰፈር ወደአቧሬ ሲሊ መሆኑ ነው። ምን አፈንዳው? ማን አፈንዳው? ለምን አፈንዳው? ይኼው "መንግስታችን"...ልቡ አድርጉልኝ መንግስታቸው አላልኩም...እስከዛሬ አልነገረንም። ከዚያ-እስከዚህ መንግስታችን ያው ወያኔ ነው።
6. ይህ በሆነ በሳምንቱ ይሆን በወሩ በሌላ ቀን ሌላ ምድር የተናውጠበት ፍንዳታ ደረሰ። የዚያን ለት ማታ ወደአምስት ሰአት ተኩል ወይም ምናልባት ከዚያ በኋላ ሳይሆን አይቀረም ። የዚያን ለት በደቡብ አዲሳባ ብኩል ያለው የመስተዋት መስኩታችን በአንድ ትልቅ ሚሳየል ተምቶ ስንጥቅጥቁ የወጣ በሚመስል ድምጽ ተናወጸና ከመኝታ ቀሰቀሰን።ደንግጠን ተነስተን ከቤቱ፣ ወጣን።፣ ጣራው ላይ ወጣሁ። ከዚህ መላው አዲስ አበባ ይታይል።ደቡቡ አዲሰ አበባ ፥ወይም የደቡቡ አዲሰአበባ ስማይ በተለያየ ቀለም ተውጦ ደም ከስማይ የሚዘንብበት ይመስላል። የፍንዳት ድምጽ በተከታይ ከፍ -ዝቅ፣ ቆም- ሐድ እያለ ቀጥሏል። የሚያስፍራ ድምጽና የሚያስፈራ ትርእይት ነበረ። ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ አላስታውስም። ዘለአለም መስሎ ተስምቶኛል። ከዘጠነኛ ክፍል ጀምሮ ዛሬም ፊልም አያለሁ። እንደዚያ አስደንጋጭ በፊልም ደርጃ እንኳን አላየሁም።
7. እንዲያ እየተመለትኩ ሰው በብዛት ወድህንጻው ሲጎርፉ አየሁና ወደታች ወድምድር ቤቱ ወረደኩኝ። የሚጎርፉው የውጭ ዜጋ ነበር። ሁሉም የሌሊት ልብስ ነው የለበሱት። በአንሶላ የተጠቀለሉ የሚመስሉ ፣ ሰቶችም ነበሩበት። አንድ ዋና ነገር ቢኖር መደበኛ ልብሱን የለበሰ አልነበረም።እዚህ ሸሽተው መምጣታቸው ነው። ይህ ህንጻ ከኔና አንድ ሁለት ቤተሰብ በቀር በሙሉ ኗሪው የውጭ አባዛኛው የዲፕሎማቲክ ኮር አባላት ናቸው። በውጭ ገንዘብ የሚከራይ ህንጻ ስለነበረ ነው።
8. ይህንንም ቁጣና መአት ማን እንዳወረድብን "መንግስታችን" እስከዛሬ አለነገረንም። አንድ በቁርጥ የሚታወቅ ነገር አለ። አነዚህን ሁለት የመሳሪያ ግምጃ ቤቶች ወያኔ ከተረከበ ከቀናት በኋላ ነበር የፈንዱት። ፪+2=4(ሁለትና ሁለት ሲደመር) ሁሌም አራት ላይሆን ይችላል። ሁለት ሙዝና ሁለት ቡርቱካን ሲደመር እንደማለት.....። በዚህ፣ በፍንዳታው ግን 2+2=4 ነበር። የሌላውን ባልወቅ ለኔ!
9. ሌላው ደግሞ ፊት በር በካዛንቺስ በር በኩልና በሰበታ በር ተቃጥሎ የቀሙ ታንኮች ነበሩ። ለዚህ ወያኔ በኦፊሴል ምን መግለጫ እንደሚሰጥ በውቀቱ ጠብቄ ምንም አልስማሁም። ከነበረም አምልጦኛል ማለት ነው። ለብዙ ጊዜ እንደዚያ ስለቆየ ባየሁት ቁጥር ያስቀኝ ነበር። ብዙ ባህርያት፣ ብስለትና ጥራት የሚጎደለው የስድስተኛ ክፍል ተደትራችንን ያስታውስኛል። ነገረ- አለሙማ ወያኔ የደርግን ወታደር ተዋግቼ ታንክ ሁሉ አቃጥየ አዲስ አበባን ....ለማለት ነው..ትያትሩ ሰሚሚ ተመለካችም ስላጣ አልገፍበትም። እንደዚህ በተኮላ ሀጎስ ቀያሽነት አፍሪካ እንድነት ድርጅትን...የኢትዮጵያ አየር መንገድን..የተባበሩት መንግስታት ጽሀፈት ቤትን እዘጋለሁ ብሎ መግለጫ እንዳወጣው ማለት ነው። ሰሚ አጣ እንጅ ተናጋሪ የነበረው ነገር ቢኖር "የወያኔን አይን እንይን!" የሚለው

*ነበር ደምቆ የታየው። እኔ እንደማስታውስው ማለት ነው። ይኸው ለአስራ ምናምን አመት እስኪያቀረን (ይቅርታ ለጸያፍ ቀንቋየ)አየነው።*

*10.አሁን ታዲያ በየቦታዎ ቦንብ ይፈንዳል። ይገርመኛልና ያለፍውንም ያስታውሰኛል። ስለዚህ ጥቂት ማለት ፈለግሁ።*

- *አንድ "ወታደር"፥ አንድ የጦር አባል በጠራራ ፀሐይ ከተማ ለከተማ ሕዝብ በሞላበት ቦታ ሁሉ የአስቸኳይ ጊዜ፥የከተተና የጦርነት አዋጅ ባልታውጀበት ቦታ ቦንብ ታጥቀ ሲሐድ ያየሁት/የስማሁት ወያኔ መንግስት ከሆነ በኋላ ነበር።በለየለት በወታደሩ መንግስት በድርግም ቢሆን ቦንብ ታጥቀ መጠበቀያውን ፈቶ የሚዞር አላየሁም።በዚህ ድርጊት የወያኔ ዘማኗ ኢትዮጵያ በአለም ላይ ብቸኛው አገር መሆን አለባት በየ እገምታለሁ። እገምታለሁ ይሰኘኝ እርገጠኛ ጥናት ስለአላየሁ ነው። ሌላው ልቤ ደግሞ ይህ ምን ጥናት ይፈልጋለ የታወቀ የተረጋገጠ ነገር አይደለም ወይ? ይለኛል*
- *ከዚያ በፊት በሲብል እጅ ስለቦንብ የስማሁት ሲነማ አምፒር የፈንዳውና ሚጪ ቱለማ የተላከከበት ነው።ለዚያ ሰበብ አድርገው ያቀረቡት የመቶአለቃ ማሞ መዝምርን ነበር? ያም ቢሆን መንግስት ያድርገው ወይ ማሞ ምንጩ የወታደር (የመንግስት)ግምጃ ቤት ነበር።*
- *ሌላው ብላታ ታከለ ወልደሐዋሪያት በቀኀስ ላይ ሙከራ ለማድረግ በሰበታ መንገደ ቀበረዋል የተባለው ቦንብ ነው።ያም ቢሆን ከመንግስት ግምጃ ቤት አውጥቷል የተባለ መኮንን የተያዘ ይመስለኛል። ሲቀይና እርጅና ሲመጣ ነገር ይዘነጋል ለማለት ነው።*
- *ኮሎኔል መንግስቱን ለመግደል ኢሒአፓ በየቦታው ያፈንዳው አለ። ያም ቢሆን ከመንግስት ግምጃ ቤት የውጣና ማን እንዳወጣው ተታወቀና የተረጋገጠ ነው።*
- *አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ህንጻ ላይ እነመለሰ ያየፈነዱት ቦንብ ምንጩ ወያኔ ነው። ማስርጃው ይኸው ዛሬ አቶ መለሰ ዜናው "መለስ " ስማቸውን ያገኙት ለቦንብ አፈንጀው አክብሮትና ማስታወሻ ነው። በስላማዊ ሰው ሰፈር ቦምብ ማፈንዳትን ተቀበለው፥አጽድቀው ተላብሰውታልና!*
- *ከዚያ ሌላ ቦንብ በየቦታው አልፎ አልፎ እየፈንዳ ገበሬም ህጻናም ሲጎዳ እንስማ ነበር። በራዲዮ ሶነገር ማለት ነው። ያ ደግሞ በጣሊያን ጊዜ የተጣለና ሳይፈነዳ የቀረ ነውእንጅ አዲስ ቦምብ አይደለም። አዲስ ቦንብ መፈንዳት የጀመረው ወያነ ከገባ ነው። ወይም ከወያኔ ጋር ነው። ወይም ወያኔ ነው።ከሌላውማ ሌላው ቀርቶ ስጋ መጉመጃ ትልክ ካራ ሳይቀር ነው ፈተሸው የወሰዱት። ይህም የተጠርጣሪ ፍለገውን ቁጥርና ሚዳውን ያጥብልናል።*

*ያሁኑ የተያየዘ ፍንዳታ የራሱ አስቂነት ያለው ይመስለኛል። እንደተቃጠለው ታንክ ማለት ነው። ደጋገሞ መርካቶ ይፈንዳል።ወይም ተራው ሰው ሰርቶ አድሮ የሚውልበት የሚያድርበት ወይም የሚጓዝበት ቦታ ይፈዳል። ያዲስ አበባ ህዝብ እነዳማንናውም ህዝብ ጤነኛ ህዝብ ነው። ወይም በእብደት አይጠረጠርም። ወይም ምን እንደሚፈልግ እቀጩን በምርጫው አሳይቷል። ልብ አድርጉልኝ!! "ወያኔን እንቅሮ ተፍቷል!!" አላልኩም። ማለት እየፈለገኝ ጸያፍ ቋንቋ ስለመሰለኝ ተውኩት*

*ሌላው ስለመርካቶ የማውቀው ነገር አለኝ። ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ቢሮም ነበረኝ። ይ የመርካቶ ሰው ያደርገኛል።በአብዛኛው ጉራጌ ከጣሊያን... ግሪክ... አርመን.. ህንድ ...አረብ ነጻ እውጥቶ የአፍሪካ ብርቀ ማናኸሪያ ያደርገውን በቦንብ ሊያጋይ ይፈልጋል ማለት ዘበት ነው። አይፈልግም! በተጻጻሪው አሁን መርካትን ለዚህ*

ያደረስውን ሕዝብ መንቀሎና ማንግሎ  ለማስወጣት ጥረት ያደርግና የሚያደርግ ወያኔ ነው። አንድ ግልጽ ማስረጃ ብወስድ  ደርግ የቀነሰውን የሱቀ ኪራይ ወያኔ አንዳንዱን እስከ  7000% ጨመሯል። ፋሽስት ያሉት ደርግ የቀነስውን ኪራይ ማለት ነው። በዚ.ህና በጠመንጃና ታንክ ማስለቀቀ መካከል ልዩነት  ቢኖር ለስሙ እንጅ ውጤቱ ላይ አይመስለኝም። መርካቶን በማፈንዳት አኳያ  ያካባቢ ማስረጃ (circumstential evidence) ቢባል ወደውያኔ የሚዞር መሰለኛል።

ከሌላ ጋርም የሚገናኝ ይመስለኛል። ወያኔ ”በሰው ዘር ማጥፋት ” ጭምር ያሳራቸውን ኢትዮጵያዊያን ጉዳይ ላይ ተኛቷል። ክሱም አከሳሰሱም ህጋዊ አለመህን ብቻ ሳይሆን ጭፍንነትና  መሐይምነት ያለው ይመስላል፤ ራሱ ወያኔ እንኳን ቢሆን “የዘር ማጥፋት ወስንጀል” የፈጸመው ጥቂት ነው። ያኔ እንደገባ በአርሲ ሀረርጌና ኢሉባቦር የፈጸመና አሁን ጋምቤላ በአኙዋኩች ላይ የሚፈጸመው “የዘር ማጥፋት” ነው። ለዚህ አንድና ሁለት የለውም። እንጅማ የቀረው የግፍ ጭፍጨፋ እንጅ ዘር ማጥፋት አይደለም። ዘር ማጥፋት የራሱ የተለየ የህግ ትርጉም ያለው በተለይ ከሁለተምኛው ያለምም ጥርነት ምክንያት የጎላ የፖለቲካና የሕግ ጽንሰ ሐሳብ ነው። ነ ናዚ ችበተለየም በአይሁዶችና  ጂፕሲዎች  (ሮማ)፣ ላይ በፈጸመው  አንድን ብሔር በእማነቱ ወይም በደሙ መርጦና ለየቶ ከመፍጀት ጋር የተገናኘ ነው።

ድንጋጤና ግራ መጋባትም ያለበት ይመሰለኛል። አሁን ጋዜጠኛውን ጎሾ ሞገስን የማሳሰሉትን ከመኝታ ቀስቀሶ ከቤትህ ጠማንጃን ቦንብ ተገኝቷል ማለት የድንቁርና የድንጋጤን የግራ መጋባት ምልክትጭመር ይመሰለኛል። ቦንብና ማሳሪያ የት እንዳልሚገኝ ለማሳየት የሞከርኩ የምስለኛል።

አሁን የወያኔ ዋናሮው ትኩረት  ሌላ ይመሰለኛል። በሱ ቤት ፥ በሱ ቤት ማለት ባቶ መለሰ ዜናዊን ቤት ማለት ነው (ወያኔ=መለሰ ዜናዊ በሚለው ቀመር መሰረት) በሱ ቤት ብልጠት መሆኑ ነው።የነዚህን የታጉርቱን ሰውች ጉዳይ“ የትላንት ዜና” አድርጎ ለዛሬ የሚወራ ሞቅ ያለ ለመሰጠትም ይመሰለኛል። ለዚያ መድህኒቱ የዛሬ ዜና ማፍጠርር ነው። ቦምቡ  ቦቡ የዛሬ ዜና መሆኑ ነው።

ለላው ፍርዱ በቱን ቃሊት መውሰድ ነው።  ክሱ መንደር እንዲታይ ሲደርግ ነገሩም የዚያኑ ያክል የመንደር ይሆናል ብሎ ማሰብ ይመስለኛል። ያስጎንዋ  ተረት ያስታውሰኛል።።።አሸዋ ውስጥ አንገቷን ትቀብራለች አሉ። እዳኙ እንዳያያት!! ረዥም አንገት ቢኖራትም አዙራ አታይም ለማለት ነው።

ሌላው “ጅቡ መጣብህ !” ለማለት ነው። ልጆች አልቀሰው ሲያስችግሩ ለጊዜው ማስታገሻ ወልጆች የሚጠቀሙብተ ዜዴ ነው። ለጊዜው እስኪነጋ ነው። እንጅ ይነጋልም ልጆቹም ያድጋሉ! ወያኔ “… ቦንብ የሚያፈንዳ ከሻአቢያ ጋር   ጋር የተገኛኘም ጠላት አለና …”ለማለት እስቦ ይመስለኛል። እንደነገርኳችሁ ….የነገርኳችሁ ይመስለኛል…ካልሆነም …ወያኔ አዋቂነት …አመዛዛኝነት…አርቆ ተማልካችነት …ራእይ …ይሉኝታ የሚጎድለው ይመሰለኛል። ብልጠት አለኝ ብሎ ይገምታል! አያጣምም! … ወይም ብልጥ የሆነ ይመስለዋል..ብልጠት ደግሞ ..ርቁ መንገድ አይወስድም!

በነገራችን ላይ ..የረሳሁትን አስታውስኩኝ። ወያኔ ያሁንን ዙር  ጭፍን ጭፍጨፋን ማጎር ሲጀምር የጀመረው በኔ መሰለኝ። “በሰው ዘር ማጥፋት ” 16 አመት ፈርዶብኛልና አነበብኩት። እስቲ  አሁን ከተያዘው “ማጣዱ ላይ ካለው” የዙሀን ትግል ጋር እንዳይሻማ ብየ በአርምሞ ይዠዋለሁ። እስቲ አንድ ከነአካቴው ማጋለጫ (Test Case)ለማድረግ ነው።ይህ ወያኔ በሰውና አገር  ላይ የሚያወርደው ክስ ሁሉ <u>የእውነትና የህግ መሠረት ያሌለው መሆኑንኑ</u>ን በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ደረጃ ሊታይ የሚቻልበትን መንገድ እያጠናሁ እያስጠናሁ ነው።ከAmnesty Internationalና Human Right Watch ሌሎችም ተመሳስይ ማሳሳይ ድርጅቶች

***ጋር ተቀረርቦ በመመካከር ላይ ነኝ።ደርግ እሰር ቤት ከ10 አመት በላይ ሲማቅቀም እነዚዚህ ድርጅቶች ተማጋቾቼ ነበሩና።***

***አቶ መለሰ ዜናዊ እስከዛሬ ካደርጉት አንድ የውደድኩላቸው ነገር አለ። የወያኔ ባለስልጣናት ዘራፊ ናቸው ያሏቸውን በስም ማጥፋት ወንጀል ለመክሰስ ገንዘብ ከፍለው ጠበቃ ገዝተው ከጨርሱ በኋላ ተውት አሉኝ። ይህ ያዋቂነት ምልክት ነው። ያላስቡት/ያልጠበቁት ሁሉ ሊወጣ ይችል ነበር!***

***በተረፈ ለውያኔ አሟሟቱን እንዲያስምርለት ልጸልይ ይሆን? ያማረ ሞት ምን ይመስላል?***

**Saturday, May 13, 2006**